# ሳንባ ነቀርሳ (TB) ማጥፋት

## *ሳንባ ነቀርሳ፤ አጠቃላይ መረጃ*

### ሳንባ ነቀርሳ ምን ማለት ነው?

ሳንባ ነቀርሳ (TB) በጀርም አማካኝነት የሚፈጠር በሽታ ሲሆን በአየር አማካይነት ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍ በሽታ ነው። ሳንባ ነቀርሳ ብዙውን ጊዜ ሳንባን የሚያጠቃ ሲሆን ሆኖም ሌሎች የሰውነት አካላትንም ፤ ጭንቅላት፣ ኩላሊትና አከርካሪን ጭምር ያጠቃል። በሳንባ ነቀርሳ የተያዘ ህክምና ካለገኘ ሊሞት ይችላል።

### ሳንባ ነቀርሳ (TB) ምልክቶች ምንድን ናቸው?

ሳንባ ነቀርሳ (TB) ህመም አጠቃላይ ምልክቶች የህመም ስሜት መሰማት፣ እቅም ማነስ ፣ ክብደት መቀነስ፣ ትኩሳት፣ እና በሌሊት በላብ መዘፈቅን ያጠቃልላል። ሳንባ ነቀርሳ (TB) የሳንባ ህመም ምልክቶች ሣል፣ የደረት ህመም እና ድም የተቀላል አክታና ሳል ናቸው። ሳንባ ነቀርሳ (TB) ህመም በሌላ ሰውነት ላይ የሚታዩት ምልክቶች በበሽታው ላይ እንደተጠቃው የሰውነት አካል ዓይነት ይላያያል።

### ሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይሰራጫል?

ሳንባው ወይም ጉሮሮው በሳንባ ነቀርሳ ጀርም የተጠቃ ሰው በሚስልበት፣ በሚያነጥስበት፣ በሚያወራበት ወይም በሚዘፍንበት ወቅት ጀርም ወደ አየር ይሰራጫል። እነዚህ ጀርሞች እንደ አየሩ ሁኔታ ለብዙ ሰዓታት በአየር ላይ ሊቆዩ ይችላሉ። እነዚህ ጀርሞች ያሉበትን አየር የሚተንፍሱ ሰዎች በበሽታው ይጠቃሉ፣ ይህም የሳንባ ኢንፌክሽን መያዝ (latent TB infection) ይባላል።

### በላተንት የሳንባ ኢንፌክሽንና በሳንባ በሽታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

ላተንት የሳንባ ኢንፌክሽን ያላቸው ሰዎች የሳንባ በሽታ ጀርሙ በሰውነታቸው ውስጥ ቢኖርም ጀርሞቹ አክቲቭ ባለመሆናቸው ሰዎቹ የህመም ሁኔታ አያሳዩም ። እነዚህ ሰዎች የሳንባ በሽታ ምልክቶች አይታይባቸውም እንዲሁም ጀርሞቹንም ለሌሎች አያስተላልፉም። ሆኖም ግን ወደፊት ወደ ሳንባ በሽታ ሊቀየር ይችላል። ወደ ሳንባ በሽታ እንዳይቀየር መካላከያ ህክምና እንዲያደርጉ ብዙውን ጊዜ ይደረጋል።

በሳንባ ህመም የተያዙ ሰዎች አክቲቪ በሆኑ ጀርሞች አማካኝነት የታመሙ ናቸው።ይህም ማለት በሰውነት ውስጥ እየተባዙ የሰውነት አካላትን ያጠቃሉ።

በአብዛኛው የሳንባ ህመም ምልክቶችን ያሳያሉ። በሳንባ ህመም የሳንባ እና የጉሮሮ በሽታ የተያዙ ጀርሞችን ለሌሎች የማሰራጨት ችሎታ አላቸው። የሳንባ በሽታን የሚከላከሉ መድሀኒቶች እንዲወስዱ ይደርጋል።

### ላተንት የሳንባ ኢንፌክሽን ያላቸው ሰዎች ጋር የተወሰን ጊዜ ያሳለፍኩ ከሆነ ምን ማደረግ ይኖርብኛል?

ላተንት የሳንባ ኢንፌክሽን ያላው ሰው የሳባ በሽታን አያስተላልፍም። ላተንት የሳንባ ኢንፌክሽን ያላቸው ሰዎች ጋር ካሳለፉ ምርመራ ማድረግ አያስፈልግዎትም። ሆኖም ግን የሳንባ በሽታ ከያዘው ወይም የበሽታው ምልክቶች ከያዛቸው ሰዎች ጋር ያሳለፉ ከሆነ መመርመር ያስፈልጋል።

### የሳንባ በሽታ ያላቸው ሰዎች ጋር ያሳለፍኩ ከሆነ ምን ማደረግ ይኖርብኛል?

የሳንባ በሽታ ያላቸው ሰዎች አብረዎቸው ብዙውን ጊዜ ወደ ሚያሳልፎቸው ሰዎች ፤ የቤተሰብ አባላትና የስር ባልደረቦች በሽታውን የማስተላለፍ እድል ይኖራቸዎል። በሳንባ በሽታ ከተያዘ ሰው ጋር ሆነው የሚያውቁ ከሆነ ወደ ዶክተርዎ ወይም የአካባቢው የጤና ዲፖርትሜንት ቢሮ በመሄድ መመርመር አለብዎት።

### የሳንባ በሽታ ምርመራ እንዴት ያደርጋሉ?

የሳንባ በሽታ ኢንፌክሽን መኖሩን ለማወቅ የምርመራ ዘዴዎች አሉ፤ የቆዳ ላይ ምርመራ ወይም የደም ምርመራዎች። የማንቶክስ ቱዩበርሱሊን (Mantoux tuberculin) የቆዳ ምርመራ የሚካሄደው፣

ቱዩበርሱሊን(tuberculin) የተሰኘ ፈሳሺ በእጅ ከክርን በታች በሚገኝ ቆዳ ላይ በመከተብ ምርመራው ይካሄዳል። ይህ የቆዳ ክትባት የተሰጣው ሰው ከ48 እስከ 72 ሰዓታት ባለው ጊዜ ውስጥ የሰለጠነ የጤና ባለሞያ በእጅዎ ላይ የሚታየው ክትባት እንዴት እንደሆነ ይመለከታል። የሰንባ የደም ምርመራ የሳንባ በሽታ የሚፈጥሩ ጀርሞች በበሽታኛው ላይ የሚፈጥሩትን ሁኔታ ይላካል።

*(ወደ ገፅ 2)*

## የሳንባ በሽታ ኢንፌክሽን መኖሩ ከተረጋገጠ ምን ማለት ነው?

የሳንባ በሽታ ኢንፌክሽን መኖሩ ከታየ በሳንባ በሽታ በሚያመጣ ጀርም መያዙን ያመለክታል። ሆኖም ወደ ሳንባ በሽታ የተለወጠ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚያረጋግጥ አይደለም።

. ሰውየው በበሽታው የተያዘ ለመሆኑ ሌሎች እንደ ራጅ ምርመራዎች፣ የአክታ ምርመራዎችን ማድረግ ያስፈልጋል።

## Bacille Calmette–Guèrin (BCG) ምን ማለት ነው?

**ቢሲጂ**(BCG) የሳንባ ህመም ክትባት ነው። **ቢሲጂ** በብዙ አገሮች በአገልግሎት ላይ ይውላል፣ ሆኖም በአሜሪካ በአጠቃላይ በአገልግሎት ላይ አይውልም። **ቢሲጂ** ሰዎችን ከሳንባ በሽታ መሉ በሙሉ መከላከል አይችልም። የተሳሳተ የቆዳ ምርመራ የበሽታ ምልክትም ሊፈጥር ይችላል። ሆኖም ግን የ**ቢሲጂ** ክትባት የወሰደ ሰው የቆዳ ምርመራ ሊያደርግ ወይም የደም ምርመራ ሊያደርግ ይችላል።

## በላተንት የሳንባ ኢንፌክሽን የተያዘ ህክምና መውሰድ የሚያስፈልገው ለምንድን ነው ?

የሳንባ በሽታ ሳይሆን የላተንት የሳንባ ኢንፌክሽን ካለዎት የሳንባውን ጀርም በመግደል ወደ ሳንባ በሽታ እንዳይቀየር የእርስዎ ዶክተር መድሂኒት እንዲወስዱ ሊያደርግ ይችላል። የላተንት የሳንባ ኢንፌክሽን ህክምና ማድረግ አስፈላጊነት የሚወሰነው በእርስዎ የሳንባ በሽታ የመያዝ እድል ጋር የተያያዘ ነው። አንዳንድ ሰዎች በሳንባ ኢንፌክሽን ከተያዙ በሆላ ወደ ሳንባ በሽታ የመቀየሩ እድል ከሌላው ሰው የበለጠ ሊሆን ይችላል። እነዚህም በኤይድስ በሽታ የተያዙ፣ በሳንባ በሽታ ከተያዘው ጋር የተገናኙ፣እንዲሁም የተወሰኑ የጤና ችግር የሚታይባቸው ሰዎችን ይጨምራል።

## የሳንባ በሽታ ህመም እንዴት ህክምና ይደረጋል?

የሳንባ በሽታ ከ6እስከ 12 ወራት የተለያዩ መድሃኒቶችን በመውሰድ ማከም ይቻላል። የሳንባ በሽታ ያላቸው ሰዎች የተሳጠቸውን መድሃኒቶችን በታዘዘላቸው መሰረት ሙሉ በሙሉ መውሰድ አላባቸው። መድሃኒቲን ሳይጨርሱ ካቆረጡት በድጋሚ ሊታመሙ ይችላሉ። መድሃኒቲን በሚገባ ካልወሰዱ ጀርሞቹ መድሃኒቱን የመቆቆም አቅም ሊያሳድጉ ይችላሉ። መድሃኒቱን የመቆቆም አቅም ያለው የሳንባ በሽታ ለማዳን አስቸጋሪና በጣም ብዙ ገንዘብ ይጠይቃል። በአንዳንድ ሁኔታ የአካባቢው የጤና ዲፓርትሜንት ሰራተኞች ከበሽተኛው ጋር በመገናኘት በሽታኛው መድሃኒት መውሰዱን ይመለከታሉ።

ይህም በቀጥታ የመከታተል ህክምና **ዲኦቲ** (DOT) በመባል ይታወቃል። **ዲኦቲ** በሽታኛው ህክምናውን አነስ ባለ ጊዜ እንዲጨርስ ያስችለዋል።

## ተጨማሪ መረጃዎች

ሲዲሲ(CDC) ስለ ሳንባ በሽታ ጥያቄዎችና መልሶች፤
http://www.cdc.gov/tb/publications/faqs/default.htm